# *የዶ/ር ነገደ ቃለ ምልልስ ከጦቢያ ሳምንታዊ ጋር*

(ዳግሜ 3, 1997 - መስከረም 5, 1998 ዓ.ም.)

*ጦቢያ* የግንቦት 97 ምርጫ ከተጠናቀቀ ሶስት ወራት አስቆጥሩዋል። የምርጫ ቦርዱ ኢህአዴግ አሸንፋዋል በማለት አውጆ ገዥው ፓርቲ ለቀጣዩ አምስት አመት መንግስት አቋቁማለሁ እያለ ተቃዋሚዎች ደግሞ በበኩላቸው ምርጫው ከዳር እስከዳር ተጭበርብሯል ውጤቱን አንቀበልም እያሉ ናቸው። ወዴት እየሄድን ነው?

*ዶ/ር ነገደ* ወሳኝ ምእራፍ ላይ እንገኛለን። ከስድስት ወር ጀምሮ እነ አቶ በረከት በሚያብጠለጥሉት መፅሃፌ ይህንን የግንቦቱን ምርጫ ብቻ ሳይሆን በኢህአዴግ ስታሊናዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት ስር እስካለን ድረስ መከተል ስላለብን ስትራቴጂ የተባለው ዋና ገፅታ የምርጫ መስፈርቶች ተሟሉ አልተሟሉ በአማራጭ ፕሮግራም ዙሪያ ህዝባችንን በገፍ እናንቀሳቅስና ያኔ ኢህአዴግ አሸንፍኩ ለማለት ከፈለገ በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአለም አቀፋ ኮሙኒቲ ፊት መጋለጥን መርጦ ይሆናል የሚል ነበር። ከዚህ ተያይዞ የተባለው በህዝቡ እንቅስቃሴ ኢህአዴግን በህዝባዊ የትግል ማእበል እዚህ "የክስረት ደረጃ" ብየ የጠራሁት ምእራፍ ካደረስነው እንዳለፈው ምርጫ ጭ-ብ-ርብሩን አጋልጠን እንደማንበተንና ለሸፍጡ ፋታ ሳንሰጥ የህዝቡን ድል ለማስመለስ ትግሉ ሳያሰልስ መቀጠል ይኖርበታል የሚል ስትራቴጂ ነበር። አሁን እዚህ ምእራፍ ላይ ነን ያለነው። ይህ ጥሪ ስለተደረገና በምርጫው ማግስት እንዳለፈው ጊዜ አንበተንም ስለተባለ፤ የተጭበረበረ ምርጫን ህዝባችን እንዳይቀበልና እንደጆርጂያና ዩክሬይን ሰላማዊ ትግሉን መቀጠል ይኖርበታል ስለተባለ የኢህአዴግ መሪዎች ይህንን ጥሪ የአመፅ ቅስቀሳ አድርገው ሲያቀርቡት ሰንብተዋል። ጥሪው ምንም የአመፅ ገፅታ እንደሌለው ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ መልስ ሰጥቼበታለሁ እዚህ ላይ አልመለስበትም።

አሁን ያለንበት ወሳኝ ምእራፍ እዛው በዛው ቀላልም ውስብስብም ነው። ቀላል ነው የምለው እህአዴግ በህዝብ ድምፅ ከተሸነፈ በሁዋላ በሸፍጥ አሸነፍኩ ብሉዋል። ምርጫው ተጭበርብሩዋል ተብሎ የተጀመረው የማጣራት ሂደትም በኢህአዴግና በምርጫ ቦርዱ መመሳጠር ተጭበርብሮ ተኮላሽቱዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ውጤት አልቀበለውም ብሉዋል። ተቃዋሚ ሃይሎችም እንደዚሁ ይህንን ውጤት አንቀበልም የህዝቡን ድምፅ ለማስከበር እንታገላለን ብለዋል። የአውሮፓ ህብረትም እንደዚሁ ምርጫው ተጭበርብሩዋል የሚል አቋዋም ወስዱዋል። በሁለት ሳምንት ውስጥ የመጨረሻውን ሪፖርትና ሃገሪቱ ከገባችበት ቀውስ ስለምትወጣበት ዘዴ ያለንን ሃሳብ (ሪኮሜንዴሽን) እናቀርባለን ብለዋል። ምን አይነት ሃሳብ እንደሚያቀርቡ ባላውቅም ራሳቸው ተጭበርብሩዋል ያሉትን ምርጫ ውጤት ተቀበሉ የሚሉበት ሁኔታ ውስጥ አይደሉም። ቀላልና ግልፅ ነው የምለው እስከዚህ ድረስ ያለውን ነው።

በዚያው ልክ ደግሞ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ነን። ህዝቡም ከዳር እስከዳር ድምፄን ለማስከበር በማደርገው ትግል አመራር ስጡኝ እያለ እየወተወተ ይገኛል። በበኩሌ ይህ የህዝቡን ድምፅ ለማስከበር የሚደረገው ትግል ያለ አንዳች ማመንታትና ማወላወል መቀጠል አለበት ባይ ነኝ። የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ምንም አይነት የመከፋፈልና የማመንታት ፍንጭ ሳያሳዩ በህገ መንግስቱ ማእቀፍ ውስጥ ባሉት የሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልቶች ማለትም በግልፅ ለመናገር በመሬት አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፎች፤ በስራ ማቆም አድማዎች ወዘተ የህዝባችንን ድል ለማስከበር ለመታገል መቁረጣቸውን ደግመው ደጋግመው ማወጅ አለባቸው። እዚህ ላይ በጣም ግልፅ መሆን ያስፈልጋል። ይህ ፀረ ሰላም ጥሪ አይደለም። በዚህ ጉዳይ በመፅሃፌ ላይ ያልኩትን እንድጠቅስ ፍቀዱልኝ

*" ህዝባችንን ቀስቅሰን ትግሉ በድል እስኪቋጠር ድረስ ታግለን እናታግል ስንል 'ግድ የለም ይሙት፤ ይታሰር፤ ይሰዋ' ማለታችን አይደለም። ይህ አባባላችን አፋኙ አገዛዝ የተወልን ምርጫ ህዝባችንን ከእለት እለት ይበልጥ እያደራጀነውና ይበልጥ እያታገልነው አፈናንና ወከባን በተሻለ እየተቋቋቋመ እንዲቀጥል እናድርገው እንጂ*

*እንዴ የነብር ጅራት እያስጨበጥንና እንዴ ደግሞ እያስለቀቅን አላስፈላጊና ፍሬ ቢስ መስዋእትነት እንዲከፍል እናድርገው ማለት ብቻ ነው"* (ገፅ 181)

*በተቃዋሚው ሰፈር ያገኘነውን* (ማለትም ኢህአዴግ የፈቀደልንን) መቀመጫ ይዘን እስከ ቀጣዩ ምርጫ እንጠብቅ የሚሉ አንዳንድ ወገኖች አሉ። እነዚህ ህዝባችንን መርተው የነብር ጅራት ካስጨበጡ በሁዋላ ልቀቅ የሚሉት ወገኖች ራሳቸውን እንደ ሰላም ሃይሎች አድርገው ይቆጥራሉ። ትግሉ በሰላማዊና ህጋዊ ዘዴ እስከመጨረሻው መቀጠል አለበት የሚሉትን ሃይሎች ደግሞ ልክ እንደወያኔ/ኢህአዴግ እንደ ፀረ ሰላም አድርገው ከማቅረብ አይመለሱም።

*በኔ ግምት ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው።* ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በሃገራችንና በህዝባችን ላይ ይህ ነው የማይባል ፀረ ሀ-ዝብ አመፅ የሚጋብዘውና የዴሞክራታይዜሽኑን ሂደት አቁዋርጦ ለአስርም ለሃያም አመት ወደ ሁዋላ የሚመልሰው አቋዋም 'ለሰላም ስንል' ያገኘነውን ተቀብለን እንቀጥል የሚለው አቋዋም ነው።

*ይህ አቋዋም ሰላም አያመጣም።* የኢህአዴግ መሪዎች በህዝቡ ተገቢ ትግል ላይ በአመፅ ለመሰማራት የልብ ልብ የሚያገኙት፤ ሰራዊቱም ሆነ ፖሊሱ ያለማመንታት የሚታዘዛቸው ራሱ የህዝቡ ትግል የማመንታትና የመከፋፈል ፍንጭ ካሳየ ብቻ ነው። ህዝባችን ከዳር እስከዳርና እንደ አንድ ሰው ሆኖ ድሉን ለማስከበር ለትግል በተነሳበትና አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ምናልባት በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ በምናየው መልክ ከህዝባችን ጎን በቆመበት ሁኔታ ተቃዋሚ ሃይሎችም የአላማ ፅናትና አንድነት ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ይህ የትግል አን-ድነት ብቻ ነው በሃገራችን የወያኔን ፀረ ህዝብ አመፅ አክሽፎ ሰላምን ሊያመጣ የሚችለው። ዛሬ ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሰላም ሃይሎች ሊባሉ የሚችሉት መራራው ትግል እስከመጨረሻው ድል ይግፋ የሚሉት ወገኖች ብቻ ናቸው። በአላማ መወላወልና የመከፋፈል ፍንጭ ግን ለኢህአዴግ ፀረ ህዝብ አመፅ በሩን በርግዶ መክፈት ይሆናል።

*ይህ የማመንታት አቋም* የዴሞክራሲውን ሂደት ለአስርም ለሃያም አመት ወደ ሁዋላ የመቀልበስ አደጋ አለው። ህዝባችንን ተነስ፤ ታገል፤ ተሰዋ፤ ምረጥ ብለነው ተነስቶ፤ ታግሎ፤ ተሰውቶና መርጦ ይህንን መንግስት እንደማይፈልግ ለኛም ለኢህአዴግ መሪዎችም፤ ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲም በግልፅ አሳይቱዋል። ይህ ሆኖ ሳለ ዛሬ የኢህአዴግ መሪዎች ሽንፈትን በፀጋ ለመቀበል ስላልተዘጋጁ ግድ የለም ለአሁኑ እንለፋቸውና በሚቀጥለው ም-ርጫ እንተያያለን የሚሉ ወገኖች ያልተገነዘቡት አንድ ቁም ነገር አለ። በሚቀጥለው ምርጫ አፍ አለን ብለው ህዝባችንን እንደዘንድሮው 'ተነስ፤ ታገል፤ ተሰዋ፤ ምረጥ' ብለው ሊቀሰቅሱ የሚችሉበት የሞራል ብቃት አይኖራቸውም። ህዝባችንም ለረዥም ዘመናት ሰላማዊ ትግል፤ የምርጫ ሂደት ወዘተ በሚሉ ነገሮች እምነት ስለሚያጣ የሚያዳምጣቸውም አይኖርም።

*ጥያቄ* እንደሚታወቀው የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን የምርጫውን ሂደት አስመልክቶ አንድ ቅድመ ሪፖርት አቅርቧል። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አን-ስቶ የኢህአዴግ ባለስልጣናት በተለይ በቡድኑ መሪ በወይዘሮ አና ጎሜዝ ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ከፍተዋል። ስለዚህ ምን ያስባሉ?

*ዶ/ር ነጋደ* ከመጠን በላይ ስቶ አንዳንዴም ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት የወጣ ገፅታ መያዙ ነው እንጂ ከሰዎቹ እንዲህ አይነቱ አካሄድ የሚጠበቅ ነበር። የኢህአዴግ መሪዎች በእውነቱ ሌላ አለም ውስጥ ናቸው። ከዚህ በፊትም በአንድ ቃለ ምልልስ ላይ ከህዝባችንም ሆነ ከአለም አቀፉ ሁኔታ አንፃር ምን ያህል የህልም አለም ውስጥ እንዳሉ የጠቆምኩት አስተያየት አለ። አንደኛ ህዝቦች አይተው አይተው በግፈኞችና በአጭበርባሪ ገዥዎች ምን ያህል እንደተንገሸገሹና ምን ያህል ለትግል ቆርጠው እንደተነሱ ጨርሶ አልገባቸውም። በመሆኑም የህዝቡን እምቢተኛነት የጥቂት ቀስቃሾች ሴራ ውጤት አድርገው ከዚያም አልፈው በአንድ መፅሃፍና በአንድ ግለሰብ እንደተጠነሰሰ 'ሴራ' አድርገው ለማቅረብ እስካሁን እየሞከሩ ናቸው። አሁን በግልፅ እንደምናየውና እነሱም አይን ካላቸው እንደሚያዩት ከሆነ ግን ከተቃዋሚ መሪዎች ይልቅ ድምፄን አስከብራለሁ ብሎ በቁርጠኝነት የተነሳውና መሪዎቹን ለትግል በመገፋፋት ላይ ያለው ህዝባችን ነው።

በአለም አቀፍ ደረጃም ያለው ይኸው ነው። ከዚህ በፊት እንዳልኩት አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ለተጭበረበሩ ምርጫዎች ያለው ትእግስት ጨርሶ ተሟጧል። ይህ ጨርሶ ስላልገባቸው የጠበቁት የታዛቢዎች ሪፖርት እንዳለፉት ምርጫዎች አሁንም "እዚህ እዚህ ትንሽ ህገወጥ ነገሮች ታይተዋል፤ እዚያ ላይ ትንሽ አላግባብ የሆነ ነገር ተፈፅሟል' የሚል አሻሚና ለማወናበድ ቀዳዳ የሚሰጥ ሪፖርት ነበር። የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ምንም በማያሻማ ሁኔታ የተደረጉትን ሸፍጦች አጋልጠው ምርጫው ዴሞክራሲያዊ አልነበረም ብለው የደረሱበትን ድምዳሜ ይፋ አደረጉ። ይህ በአለም አቀፍ ደረጃ የተደረገውን በጎ ለውጥ የሚያንፀባርቅ እርግጥ አዲስ ነገር ነው። የኢህአዴግ መሪዎች ግን በራሳቸው በቅዠት አለም ውስጥ ስለሚኖሩ ነገሩን እንዲህ አርገው አላዩትም። የችግሩ ሁሉ ምንጭ እና ጎሜዝ ናቸው ብለው በአለም አቀፍ ደረጃም ነገሩን በአን-ድ "ሃና ጎበዜ" ብለው በጠሩዋቸው ግለሰብ ላይ ለጥፈው እሳቸው ላይ ደግሞ አሳፋሪ የሆነ ዘመቻ ይዘዋል።

*ጥያቄ* ኢህአዴግ ለማሳመን እንደሚሞክረው ይህ ሪፖርት የተቃዋሚዎች ቅስቀሳ ውጤት ነው? ወይስ ታዛቢዎቹ ራሳቸው የደረሱበትን መደምደሚያ ነው ይፋ ያደረጉት?

*ዶ/ር ነገደ* እርግጥ የተቃዋሚ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላው ከማንም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገኑ የሃገራች ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች በአውሮፓም በአሜሪካም ይህንን ምርጫ በማስመልከት በታዛቢዎችም ሆነ በዲፕሎማቶች ዙሪያ የተቻለውን ያህል ለመስራት ሞክረዋል። ነገር ግን ይህ ሙከራ "ያልተጭበረበረ ምርጫን ተጭበርብሯል ብላችሁ መስክሩልን" የሚል ይዘት ፈፅሞ አልነበረውም። በአውሮፓ የተካሄደው ቅስቀሳ ባለፉት ምርጫዎች ታዛቢዎች እንታዘባለን ብለው መጥተው የኢትዮጵያን ህዝብ ትዝብት አትርፈው የሄዱበት ሂደት እንዳይደገም የሚወተውት ቅስቀሳ ነበር። በሰኔ ወር በአውሮፓ ፓርላማ አድርጌ በነበረው ንግግር ላይ ባለፉት ምርጫዎች ታዛቢዎች የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዳልተጫወቱና አንድ ጊዜ ምርጫው "ቴክኒካሊ ትክክል ነበር" ሌላ ጊዜ ደግሞ "ከአመፅ የፀዳ ሰላማዊ ሂደት ነበር" እያሉ ያሾፉበትን ፋይዳ ቢስ ሂደት አውስቼ ነበር። ከዚህ በተቀሰመ ትምህርት ይህ አይነቱ በህዝብ ትግል ማሾፍ እንዳይደገም የመቀስቀስ ሃላፊነት ስላለብን የታዛቢዎቹ ቡድን ከአውሮፓ ከመንቀሳቀሱ በፊት ያለእንዳች ማመንታት ያየውን በሃቅ እንዲመዘግብና ይፋ እንዲያደርግ ተደጋጋሚ ጥሪ አድርገናል። ለምሳሌ ኢትዮጵያውያን ከመላው አውሮፓ ተጠራርተው በአውሮፓ ፓርላማና በኮሚሽኑ ፊትለፊት እጅግ ደማቅ ሰልፍ አድርገው የተለያዩ ባለስልጣናት ጋር ተገናኝተው ለህዝባችን ፍትህ ጠይቀዋል። እነዚህ ጥሪዎች ባለፉት ምርጫዎችም ተደርገው ነበር። ግን ያኔ ለምን አልተደመጡም? ዛሬ ለምን የባእዳንን ጆሮ አገኙ? ነገደ ጎበዜና 'አና ጎበዜ' የተባሉ ሁለት 'ሴረኞች' በመግጠማቸው ሳይሆን በሁለት ምክንያቶች ነው።

አንደኛውና ዋናው ምክንያት ታዛቢዎች በሙሉ በዚህ የምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ ከፍተኛ መስዋእት እየከፈለ የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳየው ጨዋነትና ቆራጥነት እንዲሁም በዴሞክራሲው ሂደትና በራሱ ሃያልነት ያሳየው የመተማመን መንፈስ እጅግ በጣም አስደንቁዋቸዋል። እንኳን የተጭበረበረ ምርጫን በቸልተኛ አይ-ን አይቶ ማለፍ ይቅርና የተድበሰበሰና አሻሚ ሪፖርት ማቅረብን 'ይህንን የህዝብ ህልምና ጉጉት መክዳት' ያህል እንደቆጠሩት ግልፅ ነው። ይህ አድናቆታቸው በሪፖርቱም ላይ ተንፀባርቋል። ለዚህ ነው ለምሳሌ በዚህ በተባለው ሪፖርት ላይ 'ምርጫው የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ጉጉት ጋር አይመጥንም' ያሉት። ኢህአዴግ በይፋና በገፍ አጭበር-ብሮ አሸነፍኩ ባለበት ሁኔታ ከዚህ ከወጣው የለሰለሰና አሻሚ ሪፖርት ቢቀርብ ኖሮ ራሳቸው ታዛቢዎቹ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ መክዳት ይቆጥሩት ነበር። ይህንን መንገድ አልመረጡም።

ሁለተኛ የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በጭብርብሩ ማግስት በተለይ "አሸናፊም ተሸናፊም የሌለበት" ኢህአዴግንም የሚጨምር የሽግግር ዘመን መንግስት እናቋቁም በማለት ያቀረቡት ገንቢ ሃሳብ ዛሬ

ለሚታየው የውጩ አለም አቋም አስተዋፅኦ አላደረገም ማለት አይቻልም። ብዙ ባእዳን ከሶስት ወራት ወዲህ ደጋግመው የሚያነሱት የነበረው አንድ ሃሳብ ነበር። ኢህአዴግ በግልፅ ተሸንፋዋል ነገር ግን ይህንን ሽንፈት በፀጋ ለመቀበል የሚችል ሃይል አል-ሆነም። ሽንፈትን በፀጋ ለመቀበል ካልቻለ ደግሞ ሃገሪቱን ወደ አለመረጋጋት ይዞ ሊነጉድ ይችላል። የዚህ ድርጅት መሪዎች አሁን የሚገኙበት ሁኔታ 'ኮርነርድ ካት" ወይም በኛ አነጋገር አዳኝ የከበበው አውሬ አይነት ስለሆነ አንድ የሆነ ከቀውስ የመውጫ ሃሳብ አቅርቡ የሚል ግፊት ነበር። ከዚህም ጋር ተያይዞ ይህ አይነቱ የማስታረቂያ ሃሳብ በሌለበት ሁኔታ በግልፅ ምርጫው ተጭበርብሯል ኢህአዴግ ተሸንፏል ብንል ለተቃዋሚው ወገን ሾተል ማቀበልና ቀውሱን ማባባስ ብሎም ሃገሪቱን ወደ ትርምስ ለሚወስዳት ሂደት አስተዋፅኦ ማድረግ ይሆናል የሚል ስጋት ነበራቸው። በቅንጅቱና በህብረቱ የብሃራዊ አንድነት መንግስት ሃሳብ መቅረቡ ይህንን ስጋት ያነሳላቸው መሆኑና ያዩትንና የታዘቡትን በማያሻማ ሁኔታ እንዲያስቀምጡ እንዳበረታታቸው ግልፅ ይመስለኛል። ከዚህ የብሃራዊ አንድነት መንግስት ከሚል ገንቢ ሃሳብ በኋላ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አካባቢ በኢህአዴግ ጠበቅ የማለት ሁኔታ ይታያል። ሃሳቡ ከቀረበ በኋላ ለአንድ ፈረንጅ ወዳጅ ከአሜሪካ ሆኜ ደውየ ነበር። ቀደም ሲል አስታራቂ ሃሳብ የማቅረብ ሃላፊነት አለባችሁ ለተሸነፉት ለኢህአዴግ መሪዎች የመውጫ ቀዳዳ መስጠት አለባችሁ እያለ ይጨቀጭቅ ነበር። ይህ ኢህአዴግንም የሚጨምር የብሃራዊ አንድነት መንግስት ሃሳብ እንደቀረበና የኢህአዴግ መሪዎች ግን እንዳጣጣሉት ስነግረው "ከእንግዲህ ያለው የኮርነር-ድ ካት ሳይሆን የሞልቃቃ ልጅ አካሄድ (አቲቱድ) ነው።" በማለት አስተሳሰቡን በመገረም ገልፆልኛል።

*ጥያቄ* ይህ የብሃራዊ አንድነት መንግስት ሃሳብ የቀረበው የባእዳንን ጭንቀት ለማስተናገድ ነው ማለት ነው?

*ዶ/ር ነገደ ፊፅሞ አይደለም።* እርግጥ እገሪ መንገዱን በአለም አቀፍ ደረጃ ለሃገራችንንና ለህዝባችን ሰላም የሚጨነቁ ሃይሎች ያላቸውን ስጋትም የሚያስተናግድ ጥሪ ነው። ነገር ግን ይህ ጥሪ ከሁሉ በፊት መሰዋእትነት ከፍሎ በምርጫ ሂደት ድል ለተጎናፀፈው ለኢትዮጵያ ህዝብ ድሉን በሆደ ሰፊነት እንዲቀበልና የኢህአዴግንም አባላትና ደጋፊዎች አካትቶ በሃገራችን የተረጋጋ የሽግግር ዘመን እንድንከፍት የተደረገ ጥሪ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ጥሪው ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች በምርጫ ሽንፈትን በፀጋ ተቀብለው በሽግግሩ ሂደት ከኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ተባብረውና በተረጋጋ መንፈስ ለሁላችንም የምትሆን አገር እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንገነባ የቀረበ ታሪካዊ ጥሪ ነው።

እርግጥ የህብረቱ አቋም ከመጀመሪያውም አንስቶ ስለ ሽግግር ዘመን አስፈላጊነት በዝርዝር ያስቀመጠ አቋም ነው። የፕሮግራማችን ሁለተኛ ክፍል ተቃዋሚዎች በአሸናፊነት ቢወጡና የመንግስት ስልጣን ቢይዙም በሃገራችን የተዋጣለት ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ህብረተሰብ እውን ለማድረግ ስለሚጠብቁን የሽግግር ዘመን ተግባራት በዝርዝር አስቀምጧል። በዚህ ክፍል በሽግግሩ ወቅት በሚቋቋሙት ሁለት ቁልፍ አካላት ማለትም በዴሞክራታይዜሽንና በብሄራዊ እርቅ ኮሚሽኖች ተሸናፊው ኢህአዴግም ተወክሎ እንደሚሳተፍ በግልፅ አስቀምጠናል። ችግሩ እንግዲህ ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታና ከታሪክ በወረስነው አጥፊ የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ባህል ላይ የኢህአዴግ መሪዎች በምርጫ መሸነፍን የሞት ሽረት ጥያቄ አድርጎ በሚያቀርበው ፕሮፓጋንዳ የተነሳ ይህ ሃሳባችን በዚህ ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች ዘንድ ተአማኒነት አለማግኘቱ ነው። ኢህአዴግ ራሱ የዛሬ አስራ አምስት አመት ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ ከዚህ የተለየ እምብዛም አይልም ነበር። የቅስቀሳው ዋና ይዘት ሁሉንም (ማለትም የኢሰፓን አባላትም) ያካተተ የሽግግር መንግስት እናቋቁማለን ይል ነበር። ከዚያ የሆነውን እናውቃለን። በዚህ ላይ ደግሞ የታሪክ ጠባሳ አለ። ሃገራችን የፖለቲካ ስልጣን ታሪክ የአሸናፊና ተሸናፊ ታሪክ እንጂ ተቀናቃኞች በሙሉ በአሸናፊነት የሚወጡበት ሁኔታ ታይቶ አይታወቅም። በመሆኑም የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ከተሸነፍን አለቀልን ቢሉ፤ በነሱም አይን የህብረቱን የሽግግር ፕሮግራም ተአማኒነት ባይኖረው ምንም የሚያስገርም ነገር የለውም። ይህንን

ተገቢ ጭንቀት ለማስተናገድ ስንል ነው በሽግግሩ ዘመን ተቃዋሚዎች የመንግስት ስልጣን ይዘው ኢህአዴግ ግን እንደ ተቃዋሚ ድርጅት በሁለቱ ኮሚሽኖች ይሳተፍ ከሚለው አቋም አልፈን የመንግስት ስልጣን በመጋራትም ወደ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚደረገው ሂደትም የመሳተፍ ዋስትና ይሰጠው የሚል ሃሳብ ነው ያመጣነው።

*ጥያቄ* ኢህአዴግ ይህንን ጥሪ ከወዲሁ አጣጥሎታል። በአባላትና በደጋፊዎች አካባቢ ጥሪውን የመቀበል አዝማሚያ ቢታይ እንኳን የኢህአዴግ ሰራዊት ካላመነበት መሪዎቹ በዚህ አክራሪ አቫፈረኝነት የመቀጠላቸው አደጋ የለም ወይ?

*ዶ/ር ነገደ* የኢህአዴግ መሪዎች በህዝባችን ለትግል ቆርጦ መነሳትም ሆነ በአለም አቀፉ ኮሙኒቲው የተጭበረበሩ ምርጫዎች አንፃር በሚያሳየው ትእግስት አልባነት እንደተሳሳቱት ሁሉ በሰራዊቱም ጉዳይ አይሳሳቱ ስህተት እየተሳሳቱ ይመስለኛል። ሰራዊቱ የኢትዮጵያ ሰራዊት እንጂ የኢህአዴግ መሪዎች እቃ አይደለም። እውነቱን ለመናገር እንዲህ አይነቱ ስህተት እኛም ከአብዮቱ በፊት እናደርገው የነበረ ስህተት ነው። የንጉሱን ጦር የፊውዳሉ ስርአት መሳሪያ አድ-ርገን እንቆጥረው ነበር። መኢሶንም ሆነ ኢህአፓ የነበራቸው ትንተና ከዚህ ከፊውዳሉ ስርአት ሰራዊት ለኢትዮፆ ህዝብ ምንም በጎ ነገር አይመጣም። በትጥቅ ትግል መደምሰስ ያለበት ሃይል ነው የሚል ትንተና ነበር። ያን ጊዜ የተመለከትነው በሰራዊቱ ቁንጮ ላይ የነበሩት ሃይሎች የዚያ ስርአት ተጠቃሚ መሆናቸውን፤ በአምቻ ጋብቻ ተቆላልፈው በእርግጥም ያንን ስርአት ለመንከባከብና ለመጠበቅ የነበራቸውን ቁርጠኛነት ብቻ ነበር። ከስራቸው ያለው ሃይል በዚያው በህብረተሰቡ ውስጥ የሚደርሱትን ግፎችና ችግሮች እየተጋራ፤ በዚያው በህብረተሰቡ ውስጥ እየፈለቁና እየተንሸራሸሩ ያሉትን አዳዲስ ሃሳቦች እየተቀበለ ቀስ በቀስ ከፊውዳሉ ስርአት መሪዎች ቁጥጥር ስር እየወጣ ሲሄድ ማናችንም አልተገነዘብንም ነበር። እኛ ብቻ ሳንሆን የፊውዳሉም ስርአት ቁንጮዎች ይህንን በአይናቸው ስር የሚካሄድ ለውጥ ከመጤፍ አልቆጠሩትም ነበር።

ዛሬም የኢህአዴግ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ተቃዋሚዎች በዛሬ 15 አመት ዘፈን ሰራዊቱን "የኢህአዴግ ሰራዊት" እያሉ ይጠሩታል። እንደ ቅድመ አብዮቱ ዘመን ሁላችንም እየተሳሳትን ነው። እርግጥ እንደፊውዳሉ ዘመን አሁንም ይህ ሰራዊት በጥቂት የስርአቱ ተጠቃሚዎች አመራር ስር ነው ያለው። ነገር ግን ደግሞ ልክ እንደፊውዳሉ ዘመን ከታች ያለው በአጠቃላይ ከህብረተሰቡ ትግል፤ ህልምና ራእይ ራሱን ነጥሎ ለዘልአለም የሚኖር ሃይል ስላይደለ አሁንም የጥቂቶችን ጥቅምና ቅንጦት ለማረጋገጥ ወንድሙ፤ እህቱ፤ አባቱ፤ እናቱ፤ ወዳጅ ጎረቤቱ ከሚያስበውና ከሚያልመው፤ ከቆመለትና ከሚሰዋለት ህልምና አላማ ውጭ ሆኖ የሚቀጥልበት ሁኔታ ጨርሶ አይታየኝም። የወያኔ መሪዎች ህዝብን ከህዝብ በማጋጨት እድሜ ለማራዘም ሲሉ ይህንን ጦር በአመዛኙ የትግራይ ተወላጆች ጦር ለማስመሰል ይሞክራሉ። ይህ ቅጥፈት ነው። ሰራዊቱ ከመላ ኢትዮጵያ የተውጣጡ አባላት ናቸው ያሉት። ሌላም ቁም ነገር አለ። በሰራዊቱ ውስጥ በርካታ የትግራይ ተወላጆች አሉበት ብንል እንኳዋን እነዚህ በሙሉ በወያኔ ኢህአዴግ ስር ይሰለፋሉ ማለት የትግራይ ህዝብ በሙሉ በእነዚህ ሰዎች ቁጥጥር ስር ያለና ያለ ማመንታት እንደ አን-ድ ሰው ሆኖ እነሱን ይደግፋል እንደማለት ያህል በሬ ወለደ ት-ንተና ይሆናል። በትግራይ ህዝብ ዘንድ እዚህ ግባ የሚባል ድጋፍ እንደሌላቸው፤ የትግራይ ህዝብ ከቀረው ወንድሙ ከሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ ራእይም፤ ህልምም እንደሌለው እኛ በደንብ እናውቃለን። የወያኔ መሪዎችም ይህንን ስለተገነዘቡ ነው በአካባቢው ብቻቸውን ለመወዳደር የተገደዱት።

*ጥያቄ* አሁን በተቃዋሚዎች ሰፈር እየጎላ ያለው ክርክር ፓርላማ መግባት ወይስ አለመግባት በሚለው ነጥብ ዙሪያ ሆኑዋል። በተለይ የፓርላማው መከፈቻ ቀን እየተቃረበ ሲሄድ ይህ ጥያቄ እያፈጠጠ መጥቱዋል። በዚህ ጉዳይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

*ዶ/ር ነገደ* ይህንን ጥያቄ አንገብጋቢ አድርጌ አልቆጥረውም። ምርጫው ተጭበርብሩዋል። ውጤቱን አንቀበልም። የህዝብ ድምፅ እንዲከበር ሰላማዊና ህጋዊ ትግሉን እንቀጥላለን ብለናል። የህብረቱና የቅንጅቱ

አመራሮች ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላው የሃገራችን ዴሞክራቶች ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮድያ ህዝብ በዚህ ፅኑ አቋም ላይ ናቸው። የህዝቡን ድምፅ ለማስከበር ደግሞ ህዝባችን በሙሉ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ ሽፍጠኞቹን አፋጦ መያዝ ይኖርበታል። ከዚህ በመለስ ድል የሚባል ነገር የማይታሰብ ነው። ከዚህ ስንነሳ ወዲያውኑ መራገፍ ያለበት አንድ አካሄድ አለ። ሰላማዊና ህጋዊ የምንለውን ትግል ሚልዮኖች ሳይሆኑ ጥቂቶች ፓርላማ ውስጥ ገብተን በምናካሂደው 'ትግል' እንተካለን የሚሉ ወገኖች ካሉ ይህን አካሄድ በሌላ ቃል መግለፅ አይቻልም። ክህደት ነው።

ይህንን አካሄድ ካራገፍንና መጭውን ህብረተሰባችንን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ የሚደረግ ትግል የጠቅላላው የህብረተሰባችን የተለያዩ ክ-ፍሎች የጋራ ትግል ነው ብለን ለዚህ ትግል አመራር እንስጥ ብለን ከተነሳንና ትግሉን ከቀጠልን ፓርላማ የመግባት አለመግባቱ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ ጨርሶ ይቀየራል። ከዚህ አንፃር ሲታይ በኔ ግምት የሚቀጥሉት ሳምንታት ወሳኝ ሳምንታት ይሆናሉ። ወይ ይህ የህዝባችን ትግል ድል ያደርጋል። ያኔ የህዝብ ድምፅ በትክክል በተንፀባረቀበት ፓርላማ እንግባ አንግባ የሚለው ጥያቄ አይነሳም። እንገባለን። ወይ ደግሞ የህዝቡ ትግል በኢህአዴግ አመፅ ተደምስሶ፤ የተሸነፈው ህዝባችን አንገቱን በደፋበት ህብረተሰብ ውስጥ እንሆናለን። ያኔ ደግሞ በዚህ ሃገራችንንና ህዝባችንን በሸብር አንበርክኮ በሚገዛ መንግስት ፓርላማ ወስጥ "ትግሉን እንቀጥላለን" ብለው ከሚገቡ ሰዎች የኢትዮድያ ህዝብ ምንም መጠበቅ አይችልም። ሄዳ ጣፊያ የነሱዋት ታናሽና ታላቅ ስደዱልኝ እንዳለችው ሴትዮ ይሆናል። መስዋእ-ትነት በከፈለበት ህዝባዊ ትግል ያላገኘውን ድል በነዚህ ጥቂት ተመራጮች ይጎናፀፈዋል ማለት አይቻልም። በዚህ ሁኔታ የነዚህ ሰዎች እዚህ ፓርላማ መግባት ለዚህ አመፅ ቡራኬ ከመስጠት ሌላ ምን እንደሚፈይድ ለማንም ግል-ፅ አይደለም።

*ጥያቄ* አሁን አከራካሪ ሊባል የሚችለው ከአዲስ አበባ ውጭ ያለው የምርጫ ውጤት ነው። በአዲስ አበባ ቅንጅቱ ሙሉ በሙሉ አሸንፎ ቀጣዩን አስተዳደር ለመመስረት ዝግጅት እየተደረገ ነው። በተወካዮች ምክር ቤት ጉዳይ የሰጡት ትንተና ለአዲስ አበባም ይሰራል ወይ?

*ዶ/ር ነገደ* አወን ይሰራል። እንዲያውም ይብሳል። አዲስ አበባ ደሴት አይደለችም። በጠቅላላው በሃገሪቱ የህዝቡ ድም-ፅ ባልተከበረበት ሁኔታ ቢያንስ አዲስ አበባን "ነፃ እናወጣለን" ብሎ ነገር አይታየኝም። ለዚህ ደግሞ ሁለት የተያያዙ ምክንያቶች አሉ።

አንደኛው በመአከላዊ መንግስት ደረጃ የኢህአዴግ መንግስት እስካለና በዚህ ድርጅት ህገ መንግስታዊ ስርአት ስር እስካለን ድረስ በተቃዋሚ ሃይሎች ቁጥጥር ስር ያለ አስተዳደር ከወዲሁ የተኮላሸ አስተዳደር ነው። ይህንን ጉዳይ በመፅሃፌ ወስጥ በተለይ ደግሞ "ዴሞክራሲያዊ ፌዴሬሽን" ወይ-ስ ፈላጭ ቆራጭ አሃዳዊነት?" በሚለው ክፍል በሰፊው ለመተንተን ሞክሬያለሁ። ያለንበት ፌዴራል ስርአት ስታሊናዊ ፌዴራል ስርአትና ለአንድ ገዥ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የተመቻቸ ስርአት ነው። በማንኛውም የፌዴራል አስተዳደር ሊከሰቱ የሚችሉ ሶስት አይነት ግጭቶች አሉ። አንደኛ በፌዴሬሽኑ አባል መንግስታት (ማለትም በክልሎች) መሃከል ሊነሱ የሚችሉ የስልጣን፤ የድንበር ወዘተ ችግሮች አሉ። ሁለተኛ ክልሎች ከተሰጣቸው መብትና ስልጣን አልፈው ህገ መንግስቱን ሲጋፉ የሚከሰቱ ችግሮች አሉ። ስታሊናዊ ህገ መንግስታት እነዚህ ችግሮች የሚፈቱበት ስ-ርአት አላቸው። የኢህአዴግ ህገ መንግስት በአንቀፅ 62/6 እና በአን-ቀፅ 62/8 ለሁለቱ ችግሮች መፍቻ ስነስርአት አለው። ሶስተኛው ች-ግር መአከላዊው መንግስት (ማለትም ገዥው ፓርቲ) ለክልሎች የተሰጣቸውን መብ-ትና ስልጣን ሲጋፉ የሚከሰት ችግር ነው። በመፅሃፌ ላይ እንዳልኩት በስታሊናዊ የህገ መንግስት ቲዎሪ የተገነቡት " የሶቭየትም ሆነ የኢህአዴግ ህገ መንግስታት ሌላው ቀርቶ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ እንኳዋን መአከላዊው መንግስት (ማለትም ስልጣን የያዘው ፓርቲ) ህገ መንግስቱ ለአባል መንግስታት የሰጠውን መብት ሲጥስ አይታያቸውም። በመሆኑም ክልሎች መብታችንና ስልጣናችን በመአከላዊው መንግስት ተደፈረ ሲሉ የት ለማንና እንዴት አቤት እንደሚሉ የሚደነግግ አንቀፅ የለም።

ያውም እንግዲህ አዲስ አበባን በሚመለከት የከተማዋ አስተዳደር ከቀሩት ክልሎችም ይበልጥ መብት አልባ ነው። አንቀፅ 50/3 የክልሎች ምክር ቤቶች ተወካዮች ተጠሪነት ለወከላቸው ህዝብ እንደሆነ በግልፅ

*ያስቀምጣል። የአዲስ አበባ አስተዳደር ግን በህዝብ ቢመረጥም ተጠሪነቱ ለመረጠው ህዝብ አይደለም። በአንቀፅ 49/3 መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግስቱ እንደሆነ ተቀምጧል። ያለንበት "ህገ መንግስታዊ ስርአት" በእውነቱ አስገራሚ ስርአት ነው። የአዲስ አበባ ህዝብ ድምፁን ሰጠ። ምርጫ ያሸነፈው ፓርቲ ግን ለመራጩ ህዝብ ሳይሆን ተጠሪነቱ ይህ ህዝብ አልፈልግህም ብሎ በምርጫ ለጣለው ድርጅት ነው። ማለትም አሸናፊው ቅንጅት ለተሸናፊው ለኢህአዴግ ተጠሪ የሚሆንበት ስርአት ውስጥ ነን ማለት ነው!!*

*በዚህ ሁኔታ የአዲስ አበባ አስተዳደር ህዝቡ የሚጠብቀውን አገልግሎት ለማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ በጣም ጠባብ ነው። ዛሬ በአይናችን ስር የኢህአዴግ መአከላዊ መንግስት በተቃዋሚዎች እጅ የወደቀውን የአዲስ አበባ አስተዳደር ስልጣን እየተጋፋ ወናውን እያስቀረው ነው። በተለይ የአስተዳደሩን የገቢ ምንጭ እያደረቀ በመሆኑ ነገ ህዝቡ የሚጠብቀውን አገልግሎት ለማቅረብና ሌላው ቀርቶ ቆሻሻ ለማንሳት እንኳዋን የማይቻልበት ደረጃ የምንደርስበት ሁኔታ አለ። በዚህ ሁኔታ ቀፎ ቤት ገብቶ ወና ካዝና መታቀፍ ከመጣ የአዲስ አበባ ህዝብ ኢህአዴግ ይዟቸው የወደቀውን አቶ አርከበን መልሶ የሚናፍቅበት ጊዜ እንዳይመጣ እሰጋለሁ። የህዝቡ አመኔታና ትብብር ካለን ይህንን ችግር እንወጣዋለን የሚል ክርክርም ካለ ወንዝ የማያሻግር ነው። ዛሬ ህዝባችን ድምፄ ይከበር እያለ ሲታገል ይህንን ትግል ማስተባበርና መምራት ትተው ባገኘነው ድል አስተዳደሩን እንመስርታለን የሚሉት ሰዎች ይህንን ሲያደርጉ የህዝብ ድጋፍ እንደሚከፈልባቸውና አሁን ያላቸው ድጋፍ ያኔ እንደማይኖር፤ ይህ ከህዝብ መነጠል ከመጣ በኋላ ደግሞ ዞሮ ዞሮ አስተዳደሩ በህገ መንግስቱ መሰረት ተጠሪነቱ ለነ አቶ መለስ ነውና የኢህአዴግ መሪዎች ጊዜ ጠብቀው ባለፈው አስተዳደር በነ አቶ አሊ አብዶ እንዳደረጉት አሁንም አስተዳደሩን በትነው በሌሎች ሹመኞች ሊተኩ እንደሚችሉ የተገነዘቡ አይመስለኝም።*

*ከዚህ ከአስተዳደሩ መኮላሸት በተጨማሪ የህዝቡን ድምፅ ለማስከበር የሚደረገውን ትግል እንደ አልባሌ ነገር ቆጥሮ የአዲስ አበባን ውጤት ብቻ መቀበል የሚያስነሳው መሰረታዊ ጥያቄ አለ። የአዲስ አበባ አስተዳደር በተቃዋሚዎች ስለተያዘ የአዲስ አበባ ህዝብ ከቀረው ህዝባችን ይበልጥ ነፃ የሚሆንበት፤ አዲስ አበባ ከቀሩት የኢትዮጵያ ግዛቶች ይበልጥ ሰብአዊ መብቶች፤ የፕሬስ ነፃነት፤ የመደራጀት መብት ወዘተ የሚከበርባት ደሴት አትሆንም። ከነዚህ ሁለት ምክንያቶች በመንሳትና ከነሱም በላይ ደግሞ አሁን ባለው ሁኔታ ሁሉም እንደ አንድ ሰው ሆኖ የህዝቡ ድምፅ ይከበር ብሎ አጠቃላዩን ሰላማዊ ትግል ማካሄድ ሲገባው የተቃዋሚዎች የአዲስ አበባውን ውጤት መቀበል ህዝቡን ግራ የሚያጋባ፤ ለዴሞክራታይዜሽን የሚደረገውን ትግል ከፋፍሎ የሚያዳክም ስለሚመስለኝ ይህ እርምጃ መወሰድ የለበትም እላለሁ።*

*ጥያቄ ታዲያ ምርጫ ተብሎ ይህ ሁሉ የተደከመው፤ ተወካዮቼን እመርጣለሁ ብሎ ህዝቡ የታገለውና የተሰዋው ምንም ዋጋ ለሌለው ነገር ነበር ነው የሚሉን ማለት ነው?*

*ዶ/ር ነገደ* ጨርሶ እንዲህ ማለቴ አይደለም። መኢሶን ከሁለት አመት ጀምሮ የሚለው በመፅሄፌም በሰፊው የተብራራው አንድ ነጥብ ቢኖር ያለንበት ህገ መንግስታዊ ስርአት መድበለ ፓርቲ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል አይደለምየሚለው ነጥብ ነው። ተቃዋሚ ሃይሎች አዲስ አበባን ቢያሸንፉ ተጠሪነታቸው ለተሸናፊው ኢህአዴግ ነው። አንድ ተቃዋሚ ድርጅት በአንድ ክልል ቢያሸንፍ ኢህአዴግ የዚህን ክልል ስልጣን እንደልቡ ለመሸርሸርና ልክ አሁን አዲስ አበባ እንደሚያደርገው የዚያን በተቃዋሚ ቁጥጥር ስር የወደቀ ክልል አስተዳደር ቀፎውን ሊያስቀረው ይችላል። ኢህአዴግ በመሃል ደረጃ ቢሸነፍ የተከለው ህገ መንግስት-/ፖለቲካ ፕሮግራም ስለሆነ ያ የህዝብ ድጋፍ አግኝቶ የመጣ ሃይል ህገ መንግስቱን እስካልቀየረ ድረስ የራሱን ፕሮግራም ትቶ የኢህአዴግን ፕሮግራም ለማስፈፀም ለመስራት እንደሚገደድ በሰፊው ለማብራራት ሞክሬያለሁ። ይህም ሆነ ታዲያ ምርጫ ውስጥ ቅድመ ሁኔታዎች እስኪሟሉ ድረስ አንሳተፍም ማለት "ዴሞክራሲ እስኪሰፍን ድረስ ለዴሞክራሲ አንታገልም" እንደማለት ስለሚሆን ተቃዋሚ ሃይሎች አማራጭ ፕሮግራማቸውን አንግበው በሙሉ ልብ ምርጫ ውስጥ ገብተው ህዝባችንን በሚልዮን እያስቆጠሩ ማንቀሳቀስ አለባቸው ነበር የምንለው። ለምን ምርጫ ውስጥ እንገባለን? *"በዚህ*

*መድበለ ፓርቲ ምርጫ በማይፈቅድ ህገ መንግስታዊ ስርአት ስር ዛሬም ሆነ ነገ በምርጫ የምንሳተፈው መድበለ ፓርቲ ምርጫ የሚቻልበትን ስርአት ለማምጣት በተለያዩ ሰላማዊ ስልቶች የሚደረገውን ትግል ለማገዝ ነው"* (ገፅ 154)

የምርጫ ሂደት ለዚህ ለዴሞክራሲ መስፈን ለሚደረገው ህዝባዊና ሰላማዊ ትግል አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል። እዚህ ላይ የማወራው ስለ "ምርጫ ሂደት" እንጂ ስለ "ነፃ ምርጫ" አይደለም። በመፅሃፌ ላይ ነፃ ምርጫ *"ለዴሞክራሲ የሚካሄደው ተጋድሎ አይሎ ገዥዎች ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ደረጃ ሲደርስ የሚደረግ 'የድል መቋጠሪያ' ሂደት እንጂ እስከዚህም በቅድሚያ በህብረተሰቡ ውስጥ የሌለ ለዴሞክራሲ የሚያደላ አዲስ የሃይል ሚዛን የሚፈጥር ሂደት አይደለም"* ካልኩ በኋላ እንዲያውም የደቡብ አፍሪካን ፀረ አፓርታይድ ትግል ምሳሌ አንስቼ በዚች አገር መጀመሪያ እንዴት በህዝቡ የተባበረ ትግል አፓርታይድ እንደተደመሰሰና ምርጫ የተደረገው የዴሞክራሲያዊን ትግል ድል ለመቋጠር እንደሆነ አሳይቼ ነገሩ በደንብ እንዲሰመርበት በማሰብ በፀረ አፓርታይዱ ትግል ነፃ ምርጫ "የድል አጥቢያ አርበኛ" ነበር እስከማለት ሄጃለሁ።

ይህንን ሁሉ የምለው ዛሬ በህዝባችን ተጋድሎና በተቃዋሚ ድርጅቶች የበሰለ አመራር የደረስንበትን ታሪካዊ የትግል ምእራፍ አንባቢዎች በደንብ እንዲጨብጡልኝ ነው። የኔም የመኢሶንም ክርክር አማራጭ ፕሮግራም አንግበን ተንቀሳቅሰን ህዝባችንን እናንቀሳቅስ የሚል ነበር። ከዚያስ? ከዚያ በኋላ ስላለው የትግል ሂደት በመፅሃፌ ላይ *" ህዝባችን በዚህ ፕሮግራም አምኖበትና በትግሉ ወቅት ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሎለት ሳለ ኢህአዴግ በማጭበርበር 'አሸንፍኩ' ሊል ይችላል። ያኔ ደግሞ ያሻውን አማራጭ ለመምረጥ መብቱን የተነፈገውና ድሉን በሸፍጥ የተቀማው ህዝባችን በቁጣ ተነሳስቶ ትግሉን የሚቀጥልበት"* ሁኔታ ይኖራል ነበር የተባለው። አሁን እዚህ የትግል ምእራፍ መድረሳችን የማያጠራጥር ነው። የኢህአዴግ መሪዎች አመፅ አመፅ እያሉ ነጋ ጠባ የሚጮሁት በሃቅ ከተሸነፍን ይህንን ሽንፈት በፀጋ መቀበል እንደሚኖርብን ካስቀመጥን በኋላ ምርጫው ከተጭበረበረ ግን *" በግልፅ አማራጭ ዙሪያ ሳንቀሳቀስነው ህዝባችን በኢህአዴግ ስርአት ስር ፍላጎት-ህን በምርጫ ማሚሳት ሰላልቻልክ ወይ ይህ ምርጫ ተሰርዞ ሌላ ምርጫ እንዲዘጋጅ ወይ ደግሞ እንቅስቃሴህን ሳታበርድና ሌላ አምስት አመት ሳትጠብቅ አሁኑኑ በስራ ማቆም አድማ፤ በሰላማዊ ሰልፎችና በሌሎች 'የሲቪል ዲስኦቢዲያንስ' ስልቶች ትግልህን ቀጥል"* እንለዋለን ስለተባለ ነው። ይህ ደግሞ ምንም አመፅ አይደለም። መብት ነው።

አሁን ያለንበት የትግል ምእራፍ ይህንን መብታችንን በመጠቀም የህዝቡ ድምፅ ይከበር በሚለው መፈክር ዙሪያ ትግል የምናካሂድበት ምእራፍ ነው። ይህ ደግሞ ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን የዴሞክራታይዜሽን ተጋድሎ ነው። ይህ ተጋድሎ ደግሞ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የጠቅላላው የህብረተሰቡ ሃላፊነት ነው። ህብረቱ በአገር አቀፍ " የሰላም፤ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ ጉባኤ " አማካኝነት ከተደራጀ ህብረተሰባዊ ሃይል ተወካዮች ጋር ለመምከር ያቀረበው ሃሳብ ከዚህ ትንታኔ የፈለቀ ሃሳብ ነው።

*ጥያቄ* በህብረቱ ሁለተኛ ሽንጎ ለመስከረም 20 እና 21 የተጠራው አገር አቀፍ ጉባኤና ከዚያም በማግስቱ መስከረም 22 በመላ ሃገሪቱና በአለም አቀፍ ደረጃ የተጠራው ሰልፍ አላማው ምንድን ነው?

*ዶ/ር ነጋደ* ከሶስት ወር በፊት እንደነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች አማራጭ ፕሮግራማቸውን ለህዝብ እያቀረቡ በህዝብ ፊት የሚፎካከሩበት ምእራፍ አልፋዋል። ባለው ፀረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ስር ህዝቡ አማራጮችን አነፃፅሮ ይኸ ከዚያኛው ይሻለኛል ብሎ ቢመርጥም ያንን ምርጫውን እውን ለማድረግ የማይችልበት አፋኝ ስርአት ስር እንደምንገኝ ለማንም ግልፅ ሆኑዋል። ከእንግዲህ የትግሉ ዋና ገፅታ የፖለቲካ ድርጅቶች ለምርጫ የሚያደርጉት ሳይሆን በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ለዴሞክራሲ መስፈን የሚያደርገው ታሪካዊ ተጋድሎ ገፅታ ነው። የተነጠቀው የህዝብ ድምፅ ይመለስ ብለን የምናካሂደው ትግል ከእንግዲህ ሌላ ምርጫ ቢደረግ በሌላ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ አማካኝነት ይሁን፤ ሌላ ምርጫ ቢደረግ የፕሬስ ነፃነት ይበልጥ በተከበረበት አካባቢ ይሁን፤ ሌላ ምርጫ ቢደረግ መገናኛ ብዙሃን ለሁሉም በእኩል ማገልገላቸውን የሚቆጣጠር ገለልተኛ ተቋም ይመስረት፤ ከእንግዲህ ምርጫ ቢደረግ አፈና፤ ግድያ፤ ወከባ፤ እስራት የማይታሰቡ ነገሮች ሆነው ሰብአዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ በተረጋገጡበት አካባቢ ይሁን ባጭሩ

በኢትዮድያችን የተሟላ ዴሞክራሲ ይሰፈን እያልን የምናካሂደው ትግል ነው።

ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተወካዮቻው አማካኝነት በረጋ መንፈስ ተወያይተው በሚያወጡት የትግል ስትራቴጂ መሰረት ሲካሄድ እንጂ በአጠቃላይ በህብረተሰቡ የተደራጀ ተጋድሎ ሳይታጀብ የኢህአዴግና የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ተወካዮች አጋፋሪነት በር ዘግተው በሚያካሂዱት ድርድር አይደለም። በመሆኑም ከአስር አመት በፊት በተደረገው የግዮን ጉባኤ መልክ ሆኖ አሁን ግን ከዚያ በሰፋ መልክ ከየአካባቢው የሚመጡ የገበሬ፤ የሰራተኛ፤ የወጣቶች፤ የሴቶች ተወካዮች፤ የሙያና የህዝባዊ ማህበራት ተጠሪዎች፤ እንደ ንግድ ምክር ቤትና ሌሎች የኢኮኖሚ ስብስቦች፤ የሃገር ሽማግሎችና ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ የሚሳተፉበት ታላቅ ሃገራዊ ሸንጎ ሃሳብ ቀርቦ ዝግጅቱ ተጀምሩዋል። ይህንን ሸንጎ ለማዘጋጀት አንድ ግብረ ሃይል የተቋዋቋዋመ ስለሆነ ስለዝርዝር ዝግጅቱና አላማው ከዚህ አካል ማግኘት ይሻላል። ህብረቱ የዚህን ጉባኤ ሃሳብ አፈለቀ እንጂ ተሳታፊዎችን፤ አጀንዳውን ወዘተ በሚመለከት ብቻውን የሚሰራው ነገር አይኖርም። በተደረሰው ውሳኔ መሰረት ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የሲቪክ ስብስቦች ተወካዮች በዝግጅቱ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ እንዲሳተፉ ጥረት እንዲደረግ መመሪያ ተሰጥቱዋል። ግብረ ሃይሉ በተቻለ መጠን የተለያዩ ክፍሎችን በማካተት እንደሚሰራ ተስፋ አለኝ። ከያለበት የሚደርሱትን ሰነዶች አጥንቶና ከተሳታፊዎች ተወካዮች መክሮ ለጉባኤው የመወያያ ሰነድና አጀንዳ ያቀርባል ብየም ተስፋ አደርጋለሁ። ለጊዜው ስለዚህ ጉባኤ ከዚህ አልፎ መናገር አስፈላጊ አይመስለኝም። አንድ ጥሪ ማድረግ ቢያስፈልግ በሃገራችን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የተለያዩ ስብስቦች ይህንን አገራዊ ጥሪ በቅን መንፈስ ተቀብለው ጉባኤው የተሳካ እንዲሆን ከምንም አይነት ወገናዊ አመለካከት በራቀ መንፈስ እንዲሰሩ፤ ይህ አይነቱ ጉባኤ በሆነ ምክንያት አያስፈልግም ካሉ ደግሞ ለትግሉ መቀጠል ያላቸውን ሌላ ስትራቴጂ ለኛም ለኢትዮድያ ህዝብም እንዲያስታውቁ ማሳሰብ እወዳለሁ።